MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# 2ኛ የውጤት መስጫ ክፍለጊዜ 3ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በማርክ መስጫ 2 ወቅት፣ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ልብ ይበሉ፡- በ *በኢታሊክስ* የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### አለካከና መረጃዎች/አሃዞች

- *ስፋትን ወደ ማባዛትና መደመር ግብረቶች ማዛመድ።*
  - *በአንድ ባለሙሉ-ቁጥር የጎን ርዝመቶች ባሉት አራት ማእዘን ጡቦች በመሙላት ስፋቱን ማግኘት፣ እናም ስፋቱ የጎን ርዝመቶችን በማባዛት ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማሳየት።*
  - *የተጨባጭ-አለም እና የሂሳብ ፕሮብሌሞችን በመፍታት አውደ ውስጥ የአራት ማእዘኖች ስፋቶችን ለማግኘት የጎን ርዝመቶችን በሙሉ ቁጥር የጎን ርዝመቶች ማባዛት፣ እና በሂሳብ አስተሳሰብ ውስጥ የሙሉ-ቁጥር የማባዛት ውጤቶችን እንደ አራት ማዕዘናት የቦታ ይዞታ/ስፋት/ኤሪያ መወከል።*
  - *ሙሉ ቁጥር ያላቸው የጎን ርዝማኔዎች a እና b + c ያለው አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ስፋት የ a x b እና a x c ድምር መሆኑን በተጨባጭ ለማሳየት የጡቦች ድርድር ሙሊት መጠቀም።በሂብ አስተሳሰብ ውስጥ የማሰራጨት ጠባይን ለመወከል በስፋት ሞዴሎች መገልገል።*
  - *ስፋትን እንደ ድምረታዊ/የማከል ዉጤቶች ማወቅ። የቀጤ ዘዌዎችን ስፋት ወደ የማይደራረቡ አራት ማእዘኖች በመበታተን እና የማይደራረቡትን ክፍሎች ስፋቶች በመደመር የቀጥተኛ ፊገር/ምስል ስፋቶችን ማግኘት፣ ይህን ቴክኒክ የተጨባጭ አለም ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ተግባራዊ ማድረግ።*

### ቁጥሮችና ግብረቶች - ክፍልፋዮች

- 1/b በሚለው ክፍልፋይ *b*ን አንድ ሙሉ ወደ b እኩል ክፍሎች ሲከፋፈል በአንድ ክፍል የሚሰራው ብዛት መሆኑን መገንዘብ፤ *a*a/b*b* የሚለውን ክፍልፋይ በ1/b*b* መጠን ክፍሎች እንደተሰራ ብዛት መገንዘብ።

### ግብረቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- *እኩል ቡድኖች፣ ሰልፎች፣ እና የመለኪያ መጠኖችን የሚያካትቱ ሁኔታዎች ውስጥ የቃል ፕሮብሌሞችን ለመፍታት በ100 ውስጥ በማባዛትና በማካፋል መገልገል።*
- *ሶስት ሙሉ ቁጥሮችን በሚያዛምድ የማባዛት ወይም የማካፈል ቀመር ውስጥ ያልታወቀውን ቁጥር መወሰን። ለምሳሌ፣ በያንዳንዳቸው የ$8 \times ?$ ቀመሮች ቀመሩን ሃቅ የሚያደርገውን ያልታወቀ ቁጥር መወሰን $= 48$, $5 =$ � $\div 3$, $6 \times 6 =$*
- *በ100 አሃዞች ውስጥ የብዜት እና የማካፈል የትግባሬ ባህሪያትን እንደ ስልት በመጠቀም በቅልጥፍና ማባዛት እና ማካፈል።*
  - *$6 \times 4 = 24$ መሆኑ ከታወቀ፣ እንዲሁም $4 \times 6 = 24$ ይሆናል ማለት ነው። (የማባዛት የቦታ ቅይይር/ የውህደት ባሕርይ/Commutative property of multiplication )*
  - *$3 \times 5 \times 2$ በ$3 \times 5 = 15$፣ ከዚያም $15 \times 2 = 30$፣ ወይም $5 \times 2 = 10$፣ ከዚያም $3 \times 10 = 30$ በሚል ሊገኝ ይችላል። (የማባዛት ስብስብ ባሕርይ)*
  - *$8 \times 5 = 40$ እና $8 \times 2 = 16$, እንደሚሆን ካወቀ አንድ ሰው ብዜትን በመተንተን $8 \times 7$ እንደ $8 \times (5 + 2) = (8 \times 5) + (8 \times 2) = 40 + 16 = 56$ እንደሚሆን ማግኘት ይችላል። (ስርጭት ባሕርይ)*
- *ማካፈልን እንደ ያልታወቀ-ፋክቶር/factor ፕሮብሌም አድርጎ መገንዘብ። ለምሳሌ፣ በ8 ሲባዛ 32 የሚያደርገውን ቁጥር በማግኘት $32 \div 8$ን ማግኘት።*
- *የሂሳብ ቅርፀቶችን (በመደመር ሰንጠረዥ ወይም በማባዛት ሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኙ ቅርፀቶችን ጨምሮ) መለየት፣ እና በግብረቶች ጠባዮች በመጠቀም እነሱን ማብራራት። ለምሳሌ፣ ያስተዉሉ በ4 የሚባዛ ቁጥር ሁልጊዜም ሙሉ ቁጥር ይሆናል፣ እናም 4 ሲባዛ በሆነ ቁጥር ለሁለት ተደማሪዎች ለምን በእኩል ማካፈል እንደሚቻል ማስረዳት።*

### ጂኦሜትሪ

- *ቅርፆችን እኩል ስፋቶች ወዳሏቸው ክፍሎች መከፋፈል። የያንዳንዱን ክፍል ስፋት እንደ የጠቅላላው ክፍልፋይ አሃዱ አድርጎ መግለፅ። ለምሳሌ፣ አንድን ቅርፅ ወደ 4 እኩል ስፋት ወዳላቸው ክፍሎች መከፋፈል፤ እናም የያንዳንዱን ክፍል ስፋት የቅርፁ ስፋት 1/4 ብሎ መግለፅ።*

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፡- ስነ ፅሁፍ

- *ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና መልስ በመስጠት ምንባቡን መረዳትህ(ሽ)ን አሳይ፣ ለመልሶቹ ከምንባቡ መሰረት መሆኑን በማመሳከር።*
- *ከተለያዩ ባህሎች ታሪኮችን በማስታወስ በዝርዝር ተናገር/ሪ፤ ዋናውን መልክት ለይተህ(ሽ) አውጣ/ጪ፣ ትምህርት ሰጭነቱ፣ ወይም ግብረገብነቱን/ሞራል እና ቁልፍ በሆኑ ዝርዝሮች መልክቱ እንዴት እንደሚተላለፍ አስረዳ/አስረጂ።*
- *በታሪኩ ላይ የሚታይ ገፀባህርይ አስረዳ/ጂ (ለምሣሌ፡- መለያ ባህርያቸውን፣ የተነሳሱበትን ምክንያቶች፣ ወይም ስሜቶቻቸውን/አመለካከቶቻቸውን) እና ድርጊቶቻቸው ለሁነቶቹ ተከታታይነት/ቅደምተከተል ምን አስተዋፆ እንዳደረገ አስረዳ/አስረጂ።*
- *ቃላትንና ሃረጎች በፅሁፍ ውስጥ አገልግሎት ላይ በዋሉበት ሁኔታ ትርጉማቸውን መወሰን፣ ቀጥተኛን ቀጥተኛ ካልሆነ ቋንቋ በመለየት።*
- *ስለምንባቡ ስትጽፍ/ፊ ወይም ስትናገር/ሪ ከታሪኩ ውስጥ የተለያዩ ክፍሎችን መጥቀስ ድራማ፣ እና ግጥሞችን ምእራፍ፣ ሁኔታ/ስፍራ፣ እና ሥንኞችን/የግጥም አንጓ በመጠቀም፣ እያንዳንዱ ተከታታይ ድርጊት በቀዳሚው ላይ እንዴት እንደተመሠረተ አስረዳ/አስረጂ።*
- *አስተያየታቸውን ከተራኪው/ዋ ወይም ከገፀባህርያት መለየት።*
- *ፍሬሃሳቦቹን/ስርወ ቃል፣ የመነሻ ቦታ፣ እና ታሪኮቹ ስለተጻፉባቸው ንድፍ/ቅንብር በአንድ ደራሲ አማካይነት ስለ ተመሣሣይ ወይም የተለያዩ ገፀባይርያት የተጻፉ ቢሆንም (ለምሳሌ፡- ከተከታታይ የትረካ መፃሕፍት) አወዳድር/ሪ እና አነፃፅር/ሪ።*
- *በ3ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ/ጠንካራ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ መገንዘብ።*

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፡- መረጃዊ

- *የአንድን ጽሑፍ ግንዛቤ ለማሳየት ጥያቄዎች ማቅረብና መመለስ፣ ለመልሱ መሰረት የሆነውን ፅሁፉን በትክክል በመጥቀስ።*
- *የአንድን ጽሑፍ ዋና ሀሳብ መወሰን፤ ቁልፍ ዝርዝሮችን እንደገና መንገርና ዋናውን አስተሳሰብ እንዴት እንደሚደግፉ ማብራራት።*
- *በተከታታይ ታሪካዊ ክስተቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ሳይንሳዊ ሃሳቦችን ወይም ፅንሰሃሳቦችን፣ ወይም በምንባቡ ላይ የቴክኒካዊ ሂደት ደረጃዎችን ከጊዜው ጋር፣ ቅደምተከተል፣ እና መንስኤ/ያስከተለው ውጤት ጋር የሚዛመዱ ቃላትን በመጠቀም አስረዳ/አስረጂ።*
- *ለ3ኛ ክፍል ርእስ ወይም የአርእስት መስክ አግባብ ባለዉ ጽሑፍ ውስጥ የአጠቃላይ አካዴሚያዊና ጎራ-ተኮር የሆኑ ቃላትና ሃረጎችን ትርጉም መወሰን።*
- *ስለ አንድ ርእስ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት የጽሑፍ ባህሪያትን እና መዳሰሻ ምልክቶች (ለምሳሌ፣ ቁልፍ ቃላት፣ የጎንዮሽ መዳሰሻ/sidebars፣ ከሌላ አውታረ-መረብ ጋር አገናኝ ምልክቶችን/hyperlinks) በብቃት ተጠቀም/ሚ።*
- *የራሳቸውን አመለካከት ከምንባቡ ደራሲ/ጸሐፊ ሃሳብ ለይ።*
- *ከስዕላዊ መግለጫው የተገኙትን መረጃዎች በመጠቀም (ለምሳሌ፡- ካርታዎችን/ማፕ፣ ፎተግራፎችን) እና በንባቡ ውስጥ ያሉትን ቃላት ምንባቡን ስለመረዳትህ/ሽ (ለምሳሌ፡- የት፣ መቼ፣ ለምን፣ እና ቁልፍ የሆኑ ክንዋኔዎች እንዴት ሊሆኑ እንደቻሉ) ያለህን/ያለሽን ግንዛቤ አስረዳ/ጂ።*
- *በአንድ ርእስ ላይ የተጻፉ ሁለት ምንባቦችን በማነፃፀር በጣም አስፈላጊ ነጥቦችንና ቁልፍ ዝርዝሮችን አወዳድር/ሪ አነፃጽር/ሪ።*
- *ለ3ኛ ክፍል በአግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጂያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።*

**ቋንቋ፡- የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም**

- የ3ኛ ክፍል ርእሶች እና ትምህርትን በሚመለከት ሌሎች በሚሰጧቸው ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ የራሳቸውን ሃሳብ በትክክል በመግለጽ በልዩ ልዩ ውጤታማ ውይይቶች ላይ ተሳተፍ/ፊ።
- ድምፅ ከፍ ብሎ በተነበበ ፅሁፍ ወይም የሚታይ፣ ወይም ቃልን የሚያካትቱ በተለያዩ ሚድያና ብዙ ቅርፀቶች የቀረቡ መረጃዎች ዋነኛ ኣስተሳሰቦች እና ደጋፊ ዝርዝሮችን መወሰን።
- በ3ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት ላይ በመመርኮዝ ከተለያዩ ስልቶች በመምረጥ በውል ያልታወቀ እና የተለያየ-ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ሃረጎች ግልጽ አድርግ/ጊ።

## ጽሑፍ

### ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- አንድን አርእስት በመመርመር መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ፣ እና በተብራራ ሁኔታ ጽሑፎችን በመጻፍ ሃሳቦችን እና መረጃ/ኢንፎርሜሽን አስተላልፍ/ፊ።
- በቡድን አንድ አርእስት ለቡድኑ የጋራ የሆነ ኢንፎርሜሽን አስተዋውቁ፣ ለገለጻው የሚረዳ ከሆነ ስዕላዊ መግለጫዎችን ጨምሩ።
- በተጨባጭ መረጃዎች፣ ፍቺ፣ እና ዝርዝር በመስጠት ርእሱን አዳብር/ሪ።
- የመደምደሚያ ሃሳብ ወይም ክፍል አቅርብ/ቢ።

### ትረካ

- ገላጭ ዝርዝሮችን፣ እና ግልጽ የሆኑ የክስተት ቅደምተከተሎችን ውጤታማ ቴክኒክ/ዘይቤ በመጠቀም እውነተኛ ወይም ምናባዊ/ልበወለድ ልምምዶች ወይም ክስተቶች ላይ ትረካ ጻፍ/ፊ።
- አንድ ሁኔታ በመፍጠር ተራኪው/ዋን እና/ወይም ገጸባህሪያትን አስተዋውቅ/ቂ፤ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ የሚከሰት የክንውኖቹን ቅደም ተከተል አደራጅ/ጂ። ተሞክሮዎችን እና ክስተቶችን ለማዳበር ወይም ለሁኔታዎች የገጸባህሪያትን ምላሽ ለማሳየት፣ ውይይቶች እና የተግባር መግለጫዎችን፣ አስተሳሰብ፣እና ስሜቶችን ይጠቀሙ።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- በትልልቅ ሰዎች ምሪት እና ድጋፍ፣ አንድን ሥራ ለማከናወን እና ዓላማን ከግብ ለማድረስ ድርጅት እና እድገት አስፈላጊ መሆኑን በጽሑፍ አቅርብ/ቢ።
- ከእኩያ-ጓደኞች እና ከአዋቂ/ትልልቅ ሰዎች ድጋፍ በማግኘት እቅድ በማዘጋጀት፣ ክለሳ በማድረግ፣ እና ለሕትመት በማዘጋጀት ጽሑፍን አጠናክረህ/ሽ አቅርብ/ቢ።
- ከኣዋቂዎች ኣመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፅሁፍን (በቁልፍ ሰሌዳ ክሂሎቶች በመጠቀም) ለማፍለቅና ለማተም በቴክኖሎጂ መጠቀም እንዲሁም ክለሎች ጋር መገናኘትና መተባበር።
- በአንድ ርእስ ላይ ያተኮረ እውቀት ለመገንባት (የበለጠ ለማወቅ)አጫጭር የምርምር ፕሮጀክቶችን አካሂድ/ጂ።
- መረጃዎችን ከተሞክሮዎች ያስታውሱ ወይም ከህትመት እና ከዲጂታል ምንጮች መረጃን ያሰባስቡ፤ምንጮች ላይ አጭር ማስታወሻዎችን ይያዙ እና ማስረጃዎችን በተሰጡ ምድቦች ያቀናጁ።
- ለተለያዩ በዲሲፕሊን-ያተኮሩ ተግባራት፣ ኣላማዎች እና ታዳሚዎች ለረጅም የጊዜ መቃኖች/ማዕቀፎች  (ለምርምር፣ ማሰላሰያ፣ እና የክለሳ ጊዜ) ኣጠር ላሉ የጊዜ መቃኖች/ማዕቀፎች (ለኣንድ-ኣፍታ ወይም ለኣንድ ወይም ሁለት ቀን) ዲጋግሞ/በየጊዜዉ መፃፍ።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- በአንድ ርእስ ወይም ጽሑፍ ላይ፣ ያለፈ ልምድ በማስታወስ፣ ሪፖርት አድርግ/ጊ፣ ታሪክ መናገር፣ ወይም በትክክለኛና በተገቢ መረጃ የተደገፈ፣ ገላጭ ዝርዝሮችን፣ ለመረዳት በሚያስችል ፍጥነት በግልጽ ተናገር/ሪ።
- ለመረዳት በሚያስችል ፍጥነት የሚዋልል ንባብ፣ ስለ ትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ወይም ዝርዝር ለመስጠት አስፈላጊ ከሆነ በዓይን የሚታዩ ነገሮችን በመጨመር ደስ የሚል፣ በሚያዝናና ሁኔታ የሚማርክ፣ የታሪክ/ተረት ወይም የግጥሞች አሳታፊ የኦዲዮ ቅጂዎችን ፍጠር/ፍጠሪ።
- ስለአንድ ስራ ወይም ሁኔታ ዝርዝር ማብራሪያ ከተጠየቀ ለመስጠት አስፈላጊ ሲሆን ሙሉ አረፍተነገር በመስራት ተናገር/ተናገሪ።
- በመፃፍና በንግግር የመደበኛ እንግሊዘኛ ስዋስውና ኣጠቃቀም ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።
- በፅሁፍ የመደበኛ እንግሊዝኛ በትልቅ ፊደል ኣጠቃቀም/capitalization፣ በስርአተ ነጥብ እና በስፔሊንግ ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።

### አስተያየት

- የምትደግፍ(ፊ)በትን ምክንያት በመግለጽ በርእሶች ወይም በጽሑፎች ላይ አስተያየት ፃፍ/ፃፊ።
- ሌሎች የሚጽፉበትን ርእስ ወይም ጽሑፍ ያስተዋውቁ፣ አስተያየት ይግለጹ፣ እና ምክንያቶችን የሚዘረዝሩ ድርጅታዊ መዋቅር ይፍጠሩ
- የመደምደሚያውን ሃሳብ ወይም ክፍል ያቅርቡ።

## ሳይንስ

### የመሬት የጠፈር/ሳይንስ (Earth Space/Science)

- የመሬትን ባህሪያት ቅጥ ለመግለጽ ከማፕ/ከካርታ ላይ መረጃ መተንተን እና መተርጎም።
- በአንድ የተለየ ወቅት የሚጠበቅ የአየር ሁኔታዎችን ለመግለጽ በሠንጠረዥ ዳታ/መረጃ እና ምስላዊ አገላለጽ ተጠቀም(ሚ)።

### ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት

- ለስኬታማነት የተወሰነ መስፈርትን እና የቁስ፣ የጊዜ፣ እና የወጪ ገደብን ያካተተ አንድ ፍላጎትን ወይም መሻትን የሚያንጸባርቅ ቀላል ንድፍ ፕሮብሌም መግለጽ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ጂኦግራፊ

- የጂኦግራፊ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ/መለያ በመጠቀም በዓለም ላይ ያሉ ቦታዎችን እና ክልሎችን አወዳድር/ሪ።
- ሰዎች አካባቢያቸውን እንዴት እንደሚቀይሩት/እንደሚያሻሽሉት፣ እንደሚንከባከቡ፣ እና እንዴት ከአካባቢያቸው ጋር እንደሚላመዱ አስረዳ/ጂ።

### ታሪክ

- ህዝቦች በተለያዩ ምንጮች እየተጠቀሙ ባለፉት ዘመናት እንዴት እንደኖሩ መመርመር።

## የኢንፎርሜሽን መሠረተ ትምህርት

- የተሰጠ/የተመደበ ወይም በግል የሚያስፈልግ መረጃ መለየት።
- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት የተቀረፀ/የተመዘገበ ውሂብ/መረጃ ጥራት መገምገም እና መተንተን።
- የተፈላጊ መረጃን ግኝቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።
- የምርመራ/መረጃ መሻት ሂደት ተከታተል/ይ እና ከእውነተኛ ህይወት ጋር አገናዝብ/ቢ።
- መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅ /አዘጋጂ እና አጣራ/አጣሪ።
- የመረጃ ተፈላጊ ለማሟላት መገልገያዎችን መለየት።
- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን ካሉበት ፈልጎ ማግኘት፣ መገምገም፣ እና መምረጥ።
- ኣሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

### የሥነጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት

- ግላዊ ትርጉም ያላቸውን ትረካዎች በአእምሮ ለመያዝ ሪሶርሶችን በመጠቀም ሀሳቦችን ያብራሩ።
- አንድን ትረካ ለማስተላለፍ የስነጥበብ ሥራዎችን እና የንድፍ መርሆችን መርጠህ(ሽ) አሠናዳ/ጂ።
- የሥነጥበብ መሣሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና መሥሪያ ቦታን ሲጠቀሙ ተገቢውን ስርዓት/ሂደት እና ቴክኒክ/ዘዴ መምረጥ እና ማሳየት።
- ትረካዎችን ለማሻሻል ዝርዝሮችን በማከል እና የእጅ ሙያ በማሳየት የሥነ ጥበብ ስራዎችን ማጣራት።
- ለትረካው ምላሽ የስነጥበብ ሥራ ፍጠር(ሪ)።
- እደጥበብ የተሠራበት/የተፈጠረበት ጊዜ እና ቦታ እዉቀት ከተገኘ በኋላ ለስነጥበብ ምላሽ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል አስረዳ(ጂ)።

### የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ

- ለአውደርዕይ የስነጥበብ ሥራ መርጠህ(ሽ) የመረጥከ(ሽ)ው የአውደርዕዩን ጭብጥ የሚያንፀባርቅ መሆኑን አረጋግጥ(ጪ)።
- በርካታ ርእሶችን በማፍለቅ የስነጥበብ ትረካውን በትክክል የሚገልጸውን አንዱን ምረጥ(ጪ)።
- ታሪክን ለማካፈል/ለማጋራት የስነጥበብ አውደርዕይ/ኤግዚቢሽን ከእኩዮች/ከጓደኞች ጋር በትብብር አቅርብ(ቢ)።
- ስነጥበብ ሥራ የትረካውን ድርሰት በንቃት በመከታተል ጭብጡን/ፍሬ ሃሳቡን ግለጽ/ጪ።
- ትርጉም/ፍቺውን ለመግለጽ የተጠቀሙበትን የትርክት መሠረታዊ ባህርይ ለይተህ(ሽ) አስረዳ(ጂ)።
- የራስን የእደጥበብ ሥራ ውበት ለመገምገም የተዘጋጀ መስፈርት  በመለየት ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ዝንባሌ/ምላሽ መስጠት

- በሙዚቃ የተሰሙ ገላጭ ጠባዮችን ለመግለፅ በሙዚቃ የቃላት ዝርዝር መገልገል።
- በሙዚቃ ምሳሌ የተጻፈ ይዘት/ሜትር ለይ።
- የተለያዩ ባህሎችን የሚወክል ባህላዊ እና የተቀነባበረ ሙዚቃ እያዳመጥክ/ሽ ተወዛወዝ(ዢ)።
- ከተለያዩ የዓለም ባህሎች የሙዚቃ ምሳሌዎችን በማዳመጥ ሙዚቃዊ አካላት/ንጥረነገሮች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ግለጽ/ግለጪ። .
- በሙዚቃ ቅንብሮች/ንጥረነገሮችና ሌሎች የእውቀት መስኮች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች አስስ(ሺ)/መርምር(ሪ)።
- ለተወዛዋዦች አክብሮት ያላቸውን ተመልካቾች/አድማጮች ባህርይዮቻቸውን አስረዳ(ጂ)/አብራራ(ሪ)።
- መመዘኛ መስፈርት በመጠቀም የራሳቸውንና የሌሎችን አቀራረብ ገምግም(ሚ)።

### ሙዚቃ መጫወት

- ትክክለኛ የውዝዋዜ/የአዘፋፈን አቋም በመጠቀም ዘለግ/ዘና ባለ ድምፅ-ቅላፄ ዘምር(ሪ)።
- የተለያየ የመዝሙሮች አቅርቦት፣ ባለሁለት-ክፍል ዙሮች የሚያካትት መዘመር።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከዓለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከአጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- አንድን ዘፈን ለመጫወት ቀላል ዜማዎች ማንበብና የሙዚቃ ምልክቶች መተርጎም።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- ለተሰጠ አስቲናቶ (በቀጣይ የተደገመ የሙዚቃ ሃረግ ወይም ምት) መሳርያዎች በመምረጥ አንድ የሙዚቃ ቅንብር መፍጠር።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### የግልና የማህበራዊ ሃላፊነት

- ወደ ስኬት ግስጋሴን  እየተቆጣጠሩ ግላዊ አካላዊ እንቅስቃሴ ግቦችን ማስቀመጥና ማሻሻል።

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- ለመወርወር፣ ለመቅለብ/መያዝ፣ ወደላይ አሽከርክሮ ለመወርወር፣ የሚያስፈልጉ ችሎታዎችን አጣራ።
- በአካል ክፍሎችና በመሳርያዎች ለመምታት ተፈላጊ ክሂሎቶችን ማሻሻል።
- የራስ-በራስ-መገምገም እና ግብረመልስ በመንቀሳቀስ ክሂሎቶች መሻሻል አስፈላጊነታቸውን ማወቅ።

## የጤና ትምህርት

### የግልና የተጠቃሚ ጤና (PCH)

- የግል ጤንነትን የማሻሻል ወይም የመንከባከብ መንገድ ማብራራት።

### Safety and Injury/ደህንነትና ጉዳት (SI)

- በአደጋ ጊዜ በአግባቡ ምላሽ ስለመስጠት ያለህን/ያለሽን ችሎታ በተግባር አሳይ።
- የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶችን ለማግኘት እንዴት እንደሚቻል በተግባር አሳይ።
- የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶች ለማያስፈልጉት ዓይነት ሁኔታዎች እንዴት አግባብ ያለው ምላሽ እንደምትሰጥ/ጪ ችሎታህ(ሽ)ን በተግባር አሳይ።
- ማፌዝና ማስፈራራት የማስጨነቅ ተግባር መሆኑን እና በግለሰብ ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ ለይ።
- ሃሳብ በመናገር እና አሉባልታ በማውራት/በማሳበቅ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዳ/አስረጂ።